# ስለ ሕጽናዊነት

Tsigereda Gonfa

“ጠዋት እዚህ ፀሐይ ስሞቅ የቆረጥኩት የአውራ ጣቴ ጥፍር ለስንት ጉንዳን እራት ይሆናል? ባላርስም አበላሁ ማለት ነው…" (ረጅም ፅሁፍ!)

ባለፈው ሰሞን አንድ የዚሁ ሰፈር ጓደኛዬ “አብዛኞቹ የአዳም አድናቂዎች አያውቁትም …አይረዱትም… በሆይታና በግርታ ሌሎች ሲያደርጉ አይተው… 'እንወደዋለን' እያሉ ፌስ ቡክ ፕሮፋይል ፒክቸር ቀየሩ እንጂ… ይህንንም ለማስረዳት ከአፃፃፍ ቴክኒኩ ጋር የተያያዙ ቃላትን የሚያውቅ ካለ እስቲ ይመልስ?” የሚል አንደምታን ይዞ እነዚህን ደረደረልኝ…

ሕፅናዊነት
Black Hawk
Intertextuality
Intratextuality
Bio-Fiction
እንጀራ
ኢንጆሪ
Interconnectedness
Stream of Consciousness
መረቅ
.
ስጀምር…

#ሕፅን ለ #Intertextuality አዳም የሰጠው የአማርኛ ትርጓሜ ነው (ያነጣጠረ ትርጓሜ ላይሆን ይችላል ብሎ ቢጠራጠርም) Intertextuality አሰያየሙ እና አጠቃቀሙ ቢያከራክርም ከስነፅሁፍ ቴክኒኮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ብዙ አይነት አሰራሮች አሉት … አንደኛው አሰራር ዋናውን ታሪክ የሚያጅቡ ንኡስ ታሪኮች፤ ቁርጥራጭ መረጃዎች ፤ጥቅስ እና የህዳግ ማስታወሻዎችን ከሌሎች ሰዎች ፅሁፎች እና አባባሎችን መጠቀሙ ነው ይህም Paratextual ይባላል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ልብ ወለድ ውስጥ ሌላ ልብወለድን በመፍጠር ማነፃፀሩ ሲሆን ይህም Metatextual ይባላል፡፡ ቀደም ሲል ያነበባቸውን መፃህፍት በእውቀት ስራ ላይ ለማዋል አላማ እንደሚጠቀምበትም ይናገራል፡፡ (መረቅ ውስጥ ፍቅር እስከ መቃብርን እንደማንሳት) ብዙዎች ሲጠቀሙበት ባይታይም በሀገራችን የስነ ፅሁፍ ታሪክ እንግዳ ያልሆነ ከክብረነገሥት ጀምሮ ስራ ላይ ሲውል የነበረ ቴክኒክ ነው፡፡

#Intratextuality አጠቃቀሙ የሕፅን አይነት ሆኖ የተጠቀማቸው ደጋፊ ታሪኮች እና ቁርጥራጭ መረጃዎች ፡ የህዳግ ማስታወሻዎች እና የመሳሰሉት ግን ከሌሎች ፀሐፊዎች ሳይሆን ከዛው መፅሐፍ ከራሱ ስራ በሆነ ጊዜ… በተለይ ይህንን እቴሜቴ ሎሚሽታ ላይ የስብሀት ጢም ላይ በደማቅ(በቦልድ)የተፃፉት ኃላ ላይ ርዕስ ሆነው እንደመጡት… እንዲሁም ይወሰዳል መንገድ ያመጣል መንገድ ላይም በስፋት ተጠቅሞበታል፡፡

#Black Hawk ሎሚ ሽታን ጋቢ ደርባ ከተጋደመችበት ሶፋ አባንኖ የሚያስነሳት ጥቁር ቁራ ወይም ጆፌ አሞራ… ከነገሩ እና ከድርጊቱ ጋር በቀጥታ ባይገናኝም ስለታየ ወይም ድምፁ ስለተሰማ ብቻ የመጥፎ እድል/የመልካምም ሊሆን ይችላል/ ምሳሌ ተደርጎ መወሰዱ… በባህልም … በልማድም …በሃይማኖትም … ቀልቤ… ደመነፍሴ…ልቦናዬ… መንፈሴ እያልን ስፍራ የምንሰጠው ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ ባዶ እንስራ የያዘች ሴት…ጥቁር ድመት ቀድማ መንገዱን ካቋረጠች 'መንገድ አልሄድም' ተብሎ ከጉዞ እንደሚቀር አይነት… በተለይ ይወሰዳል መንገድ ያመጣል መንገድ ላይ ይህን መሰል አፃፃፍ በስፋት ተጠቅሟል… ሁሉም ምዕራፍ ላይ ጆፌ አሞራ አለ፡፡ ታሪኮቹ እርስ በእርስ የሚያያይዝ እና የሚያስተሳስርም ሆኗል፡፡

#Bio-Fiction በእውኑ አለም የነበሩ ወይም ያሉ ሰዎችን ስማቸው ብቻ ተቀይሮ ወይም ሳይቀየር ወደ ልቦለድ ታሪክ ማምጣት ነው፡፡ ይህም በሌሎች ደራሲዎች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ በተለይ በአሉ ግርማ በ “ደራሲው” መፅሃፉ የስብሃትን እና የተረት ሰፈርን ታሪክ በልቦለድ አለም ቁልጭ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ አዳምም እንዲሁ በ እቴሜቴ ሎሚሽታ ላይ (የስብሃት ጢም) ደራሲ ስብሃት ገ/እግዚአብሄርን እና ሰዓሊ መስኮት ገረሱን (መስኮት ገረሱ ... ደበበ ሰይፉ ነው የሚል ግምት ነበር የኋላኋላ ግን ደበበ ሳይሆን ሌላ ሰው መሆኑን አዳም ተናግሯል ... የልቦለዱ መስኮት ቁመቱ ድንክ ሰው ሲሆን የእውኑ ደበበ ግን አጭር እንጂ ድንክ አልነበረም) እነዚህን የእውን አለም ሰዎች ወደ ልብወለዱ አለም አምጥቶ ከነፋኖስ እና በረካ ጋር ያነጋግራቸዋል፡፡ እቴጌ ጣይቱንም መረቅ ላይ እናገኛቸዋለን፡፡ ግራጫ ቃጭሎች ላይ ያለው መዝገቡ ዱባለም የአዳም ልጅነት እና ወጣትነት ሊሆን ይችላል ተብሎ አንድ ወቅት ሲያወዛግብ ነበር፡፡ አዳም ራሱ “ነፋስ መውጫን አይቼም አላውቅም” ብሎ ገላገለን እንጂ::

ስቀጥል...

እንጀራ እና እንጀሪም ግራጫ ቃጭሎች ላይ በሰፊው የተተነተነ የራሱ የአፃፃፍ ስልት ነው ስለ አጀማመሩም ሲናገር “ከ8 አመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንጀራ ለመብላት ሄድኩ ሳየው አዲስ ነገር ሆነብኝ፡፡ አይቼው እንደማላውቅ ብርቅ ነገር ሆነብኝ፡፡ እናም ጥያቄ መጠየቅ ጀመርኩ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ... ሳይፃፍለት...ያለማቋረጥ ምግብ ሆኖ እስከዛሬ ቆይቷል... እንጀራ ግን ምግብ ብቻ ሳይሆን ሌላም ነገር አለው አልኩ፡፡ ከዚህ ተነስቼ የእንጀራን ቅርፅ ማየት ጀመርኩ:: ከጂኦሜትሪ አንፃር አየሁት... ስለ እንጀራ ታሪክ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ የሚገርም ነበር፡፡ እንጀራ ከእግዚአብሄር ጋር ይገናኛል፡፡ እንጀራ ከጠቢባን ጋር ይገናኛል፡ ፡ ከጥንት ጂኦሜትሪ ጋር ይገናኛል፡፡ ስለዚህ እንጀራን ሜታፈር ማድረግ ፈለግኩ፡፡ እንጀራ ውስጥ ያለው መዋቅር ላይ ወጥ ስታፈስበት መረቁ በተለያዩ አቅጣጫዎች ነው የሚሄደው እንጂ በአንድ አቅጣጫ ከ ሀ ተነስቶ እስከ ፐ አይደለም፡፡ እኔም የምፅፈው በዚህ መልኩ ነው፡፡”

ቀጥሎም ... “ላለመታየት ትንሽ የቀራት ጤፍ ወደሚታይ ሰፊ ነገር መለወጥ መቻሉ...የጤፍን አናሳነት ትንሽ ብናገናት ‘መጥፋት’ ትሆናለች፡፡ የማይታይን ወደሚታይ እንደመከሰት መሆኑ ነው ሃይማኖት ዓለምን እግዚአብሄር ፈጠራት... ሳይንስ ደግሞ ቢግ ባንግ እንደሚለው ነው... ጠረጴዛ ላይ የተኛ ነጭ ልሙጥ ወረቀትና እላዩ ላይ ተቀርፆ የተጋደመ እርሳስ እጅግ ማራኪ ምስል አላቸው ለእኔ...ምድርም ባዶ ነበረች ወረቀትም ባዶ ነበር ከነቁጥ ጀምሮ ቃላት፤ ፊደላት፤ ሆሄአት፤ ዓ.ነገር፤አንቀፅ፤ ምእራፍ... ብሎም አለማት...እንጀራ ራሱን የቻለ ሚልኪ ዌይ ሊሆን ይችላል፡፡

እንጀራ ከዳቦ ወይም ከሌሎች የሚጋገሩ ምግቦች የሚለየው በዓይኖቹ ነው... በጠጣር እና በፈሳሽ መካከል ያለ ነገር መሆኑ ነው...የተሟላ አይነት ህልውና አለው ... ይታያል.. ይቀመሳል...ይነካል ... ይበላል...፡፡ የቅርብ ታሪኩ ሊጥ ሆኖ ግን በሊጥ አይበላም፡፡ በምትኩ ወጥ እናፈሳለን... ወይም በ መረቅ እናርሳለን... ወጡ ሕፅን ነው፡፡ ማባያ ”እንግዲህ አዳም “እንጀራ ምንድነው?” ከሚለው ተነስቶ ነው ወደ Intertextuality ቴክኒክ የደረሰው፡፡ ከግራጫ ቃጭሎች በኋላም በሰፊው እንደተጠቀመበት ይናገራል፡፡ እንጀራ ሲበላ ወጥ እንጀራ ላይ ይፈሳል በዚህም በአይኑ የሚገቡ ደቃቃ የወጥ ጅረቶችን አካሄድ እና የእንጀራውን ግንኙነት የሚያጤን ነው፡፡ ድርሰቶቹ እንጀራው ይሆኑና መቼቱ (ጊዜ እና ቦታ)ዓይኖቹ... ወጡ ገፀባህሪያቱ...ገጠመኞቻቸው እና ኹነቶቻቸው...(የእንጀራ አይኖች ከላይ ሲታዩ ክፍትፍት ያሉ ቢመስሉም ውስጥ ለውስጥ ግን ግጥም እና የገናኙ ናቸው:: ልክ እቴሜቴ ሎሚሽታ ላይ ያሉ ታሪኮች በታሪካቸው ፍሰት ሳይሆን በመቼት እና በገፀባህሪ ብቻ እንደሚገናኙት)

#Interconnectednesss ፅሁፎቹ ለተደራሲው /አንባቢው ቅርብ እና በቀላሉ ለመረዳት የሚችላቸውን ነገሮች ማካተቱ...
#Stream of Consciousness እንደ ህልም ወይም ከራስ ጋር እንደ መጨዋወት ... አይነት ገፀባህሪያቱ ብቻቸውን ሆነው ወይም በሰዎች መሀል በሃሳባቸው ያለውን... በአዕምሯቸው የሚመላለሰውን 'ላድርግ አላድርግ ... ልሂድ ልቅር ... ልናገር አልናገር ...' እያሉ ከራሳቸው ጋር የሚያደርጉትን ሙግት/ ጭውውት የሚገልፅበት የአፃፃፍ ስልቱ ነው፡፡

#መረቅ #አንጓ እና #መለልታ ... መረቅ ላይ ከአራት ምዕራፎች እንደ መረቅ የተንጠባጠቡት ቃላት መጨረሻ ላይ አንጓና መለልታ ይሆናሉ፡፡ እናና ሸንኮራ አገዳ ስትመጥ አንጓውን ትወዳለች፡፡ "እንዴት አንድ መለልታ ሁለት አንጓ ይኖረዋል?" እያለ ሸንኮራ ሻጩ ዋህድ ቢያማርርም... አንጓ ማገጃ ነው፡፡ ቆም ቀጥ የሚባልበት...እልባት የሚደረግበት ...መለልታ ደግሞ ርዝማኔ ...ርዝማኔው በመረቅ የተሞላ...ያለ እልባት መፃፉ...ያለ እልባት መነበቡ...የማንበብ ሂደቱም እንጀራ መዘርጋት ... እንጀራው

ላይ ወጥ/መረቅ ማፍሰስ... በሂደቱም መጎራረስ...በመጨረሻም የቀረውን አንድ ገፅ የመረቅ ቅሬት ጠራርጎ መብላትን ያካትታል፡ ፡ "የመፅሐፍ ቀበኛ" እንዲሉ..

ስጨምር...

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጠይም እና ግራጫ አንድ አይነት ይመስሉኝ ነበር፡፡ ሁለቱም በመንጣት እና በመጥቆር መሃል ናቸው፡፡ ፅንፍ ያልያዙ ቀለማት፡፡ ለዘብተኛ ቀለማት፡፡ ማኪያቶ ነገር፡፡ ግራጫ ቃጭሎች...ግራጫ መሬት ... ግራጫ ልብስ... ጠይም ሰው... ጠይም መሬት... ጠይም ገላ... ጠይም እንጀራ... ግን የተለያዩ ናቸው፡፡ ጠይም የህይወት ቀለም ነው፡፡ ነፍስ ላለው ነገር የምንጠቀምበት ... ግራጫ ለግዑዝ (የስንብት ቀለማት ላይም እነዚህ ቀለማት በብዛት ይኖራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ በተለይ (ጠይም) ሌላው ያለ ምንም ተከታታይ ጥናት በግል ምልከታዬ ያስተዋልኩት...የአንዱ መፅሐፍ ርዕስ ሌላኛው መፅሐፍ ውስጥ መገኘቱ ነው፡፡ ቢያንስ የአንዱ፡፡

እያለ... እያለ... ይቀጥላል...

በቀረውስ ወንደሞች ሆይ ፀደይ ወንድሙ፤ ቴዎድሮስ አጥላው፤ ጌታሁን ሄራሞ እና ሌሎችም... ብዙ ብዙ ያሉለት ጉዳይ አይደለምን?...በ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ቤቱ በየዲግሪ ማሟያው ... በየጥናት ወረቀቱ... የቤተ መፃህፍት መደርደሪያዎችንስ ያጣበበ አይደለምን? ማንም ተጨማሪ ማወቅ የፈለገ...ሊያገኛቸው ይችል የለምን?

ጠያቂዬ ሆይ...!

እኔም ካጠረቃቀምኳቸው ከየጋዜጣው፤ከየመፅሄቱ፤ Adam's Word on facebook... ከየመፅሀፉቱ ... ከራሱ አንደበት የሰማሁትን ... እናም ከመሳሰሉት ያገኘኋቸውን ያሉኝን መረጃዎች በዚህ መልኩ እንዳጠናቅር ለሌሎችም እንዳካፍል ስላነሳሳኸኝ አመሰግናለሁ!...ተጨማሪ ተያያዥ ጥያቄዎች ካሉህም "ኤክስ" እና "ራይት" ሰጥቶ ለማንጓጠጥ ሳይሆን በመማማር እና እውቀትን በመፈለግ ስሜት በደስታ እቀበላለሁ...

ያልገባኝ...

አንድን አንባቢ የስነፅሁፍ ቴክኒኮችን ለማወቅ ምን ያስገድደዋል? አንባቢ እኮ ማንም ፊደል የቆጠረ እና የንባብ ዝንባሌ ያለው ሊሆን ይችላል...ከስነፅሁፍ እጅጉን የራቀ ሙያ ያለውም ሊሆን ይችላል...(ፀሐፊው አዳም ራሱ የጂኦግራፊ ምሩቅ መሆኑን ልብ ይሏል...) አንባቢው የስነፅሁፍ ትምህርት ቤት ገብቶ Theories, Principles, Methods, Concepts, Strategies... ያጠና...የጠበጠበና የሸመደደ... ፀሃፊው ማለት የፈለገውን እና የሚያስረዳበትን መንገድ ከሌሎች በተሻለ መልኩ መረዳት የሚችል ከሆነ... እሰየው፡፡ ካላወቀም ሊወቀስበት አይገባም፡፡ "የአፃፃፍ ቴክኒኩን ሳታውቅ ደራሲውን አትውደድ/አታድንቅ" ሊባልም አይችልም፡፡ ቴክኒኮቹንማ ፀሐፊዉ ይጨነቅበት...

የገባኝ...

ፌስቡክን ሳላውቅ የአዳምን መፅሐፎች አውቃለሁ...Profile Picture ፡ Cover Photo መቀየር እንዴት እንደሆነ ሳላውቅ አውቀዋለሁ... እዚህ ስመጣ ሌሎች መሰል ሰዎችን እና እሱን ራሱን አገኘሁ፡፡ ደስም አለኝ፡፡ "አዲስ መፅሐፍ ይዤ መጣሁ" አለኝ፡፡ የበለጠ ደስ አለኝ፡፡ ይኸው ነው! እንጂማ የነፋሱን አቅጣጫ ተከትዬ አቧራ የማስነሳት ፍላጎት የለኝም፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ብዙዎች ያወሩበትን ጉዳይ እኔ ዝም እልበታለሁ፡፡ አንባቢ መስሎ መታየት የሚያኩራራ ነገር አይደለም፡፡ ኧረ አንባቢ መሆን ራሱ የሚያመፃድቅ ነገር አይደለም፡፡ የዝንባሌ ጉዳይ ነው፡፡ አንዳንዶች ነገርን በማንበብ ይረዳሉ... ይዝናናሉ... ወይም ይደበራሉ... ሌሎች በተግባር በመለማመድ... በእጅ በመዳሰስ 'በመቁረጥ በመፍለጥ' ... (Technical and Vocational እንዲሉ...) የተቀሩት ደግሞ በውይይት እና በምክክር ወይም በጫወታ ነገሮችን የበለጠ ይገነዘባሉ... የተፈጥሮ ጉዳይ ነው፡፡

ማንበብ መውደድ ጥሩ ነገር ነው፡፡ አለማንበብም “ውጉዝ ከመአርዮስ” አያሰኝም፡፡ ልክ እንደዚሁ አዳምን ማንበብ … መውደድ …ማድነቅ ጥሩ ነገር ነው፡፡ አለማወቅም … አለማንበብም … አለማድነቅም ኢያስወቅስም፡፡

ስጨርስ…

እሱ በሆይሆታ እና በአጀብ በጭብጨባ ብዛት አይደምቅም… በጭርታ እና ዝምታም አይፈዝም፡፡
“A writer like a boxer must stand alone” ያለው ማን ነበር?